የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 55
ADDIS ABABA - 15th June, 1999


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፪/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የኢትዮ—ማሌዥያ የኢኮኖሚ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................... ገጽ ፩ሺ፶፫


## CONTENTS


Proclamation No. 172/1999
Ethio-Malaysia Economic, Scientific and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation .......................................... Page 1053


## አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፪/፲፱፻፺፩

## የኢትዮ – ማሌዥያ የኢኮኖሚ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በማሌዥያ መንግሥታት መካከል የኢኮኖሚ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ኩዋላ ላምፑር ላይ የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ የጸና የሚሆነውና በሥራ ላይ የሚውለው ሁለቱ አገሮች በየሕገ መንግሥቶቻቸው መሠረት አስፈላጊው ሥነ ሥርዓት ሲሟላ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮ – ማሌዥያ የኢኮኖሚ ፣ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፪/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 172/1999
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO-MALAYSIA ECONOMIC, SCIENTIFIC AND TECHNICAL COOPERATION AGREEMENT

WHEREAS, an Agreement, on Economic, Scientific, and Technical Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Malaysia, was signed at Kuala Lumpur on the 22nd day of October, 1998;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force on the date of its signing by both Contracting Parties and shall be implemented following the fulfillment of the respective Constitutional requirements;

WHEREAS, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 15th day of June, 1999;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Ethio-Malaysia Economic, Scientific and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 172/1999."

፪· የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በማሌዥያ መንግሥት መካከል እ·ኤ·አ· ኦክቶበር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ኩዋላ ላምፑር ላይ የተፈረመው የኢኮኖሚ ፣ የሣይንስና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል ።

፫· የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ሥልጣን

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement on Economic, Scientific and Technical Cooperation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Malaysia signed in Kuala Lumpur on the 22nd day of October, 1998 is ratified.

3. *Power of the Minister of Economic Development and Cooperation*

The Minister of Economic Development and Cooperation is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 15th day of June, 1999.

Done at Addis Ababa, this 15th day of June, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE